ጥር 5/2004 ዓ.ም.

# <u>በደቡብ ኢትዮጵያ የጎፋ ልዩ ዞን መኢአድ</u>

# <u>ጠቅላላ ጉባዔ አካሄደ።</u>

*<u>ከሦስት ወረዳ የመጡ ግለሰቦች የመኢአድ አባል እንዲሆኑ በሰልፍ ጉባዔውን ጠየቁ</u>*

በደቡብ ኢትዮጵያ በጎፋ ልዩ ዞን የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) የዞኑን ጠቅላላ ጉባዔ ጥር 5/2004 ዓ.ም በሳውላ ከተማ ማካሄዱን አቶ እንድርያስ ኤሮ የመኢአድ የማዕከላዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባልና የደቡብ ቀጠና ኃላፊ ለፓርቲው የህዝብ ግንኙነት ቋሚ ኮሚቴ ገለጹ።

በጉባዔው ላይ የገዥው ፓርቲ በመኢአድ አባላት ላይ እያደረሰ ስላለው ጥቃቶች፣ መኢአድ ከቀበሌ እስከ ወረዳ በምን መልክ መደራጀት እንዳለበት፣ በአሁን ወቅት ህዝቡ የኢህዴግ አገዛዝ ቀንበሩ እየከፋበት በመሄዱ ወደ መኢአድ ጽ/ቤት እየመጣ በመሆኑ ይህን ህዝብ እንዴት በጥበብ ማደራጀት እንደሚቻል እንዲሁም የኡባ ወረዳ ጽ/ቤት ግንባታ ጉዳይ የሚሉት ርዕሰ ጉዳዮች ትኩረት የተሰጣቸው አጀንዳዎች እንደነበሩ የደቡብ ቀጠና ተጠሪው አስረድተዋል።

በአካባቢው በመኢአድ አባላት ላይ በተለይም ከምርጫ 2002 ዓ.ም. ጀምሮ የገዥው ፓርቲ እየፈጸመ ያለው ግድያ፣ እስራትና ድብደባ፣ የመኢአድ አባላትን የእርሻ መሬትን መቀማት፣ ንብረትና የእርሻ ምርት ውጤቶችን በእሳት ማጋየት፣ በቤት እንስሳት ላይ የሚደረግ ግድያና ድብደባ፣ በመንግሥት ሠራተኞች ላይ እየደረሰ ያለው አድሎአዊ አሠራር፣ ዛቻ እና ሌሎችም ጥቃቶች በዝርዝር በጠቅላላ ጉባዔተኛው ውይይት የተካሄደባቸው መሆኑን አቶ እንድርያስ ጠቅሰዋል።

በኡባ ወረዳ የመኢአድ ጽ/ቤት ለመገንባት በተያዘው ዝግጅት ወረዳዎች የገንዘብ፣ የቁሳቁስ፣ የዕውቀትና የጉልበት ድጋፍ እንደሚያከናውኑ ለምሳሌም ያህል የአናፂነት ሙያ ያላቸው ሰባት የአመራር አባላት በነጻ ጽ/ቤቱን እንደሚሠሩ መስማማታቸውን እና ሁሉም ወረዳዎች የየበኩላቸውን ትብብር ለማድረግ ቃል መግባታቸውን የደቡብ ቀጠና ኃላፊው ለመኢአድ ህዝብ ግንኙነት ቋሚ ኮሚቴ አብራርተዋል።

እንደ አቶ እንድርያስ ገለጻ የዕለቱን ጉባዔ የተለየ ከሚያደርጉት ጉዳዮች አንዱ ‹‹ስብሰባችንን እንዳጠናቀቅን ከሦስት ወረዳዎች የመጡ አስራ ስድስት ግለሰቦች የመኢአድ አባል እንሁን፤ አደራጁን ብለው በሰልፍ ሆነው የጠየቁን አጅግ ልባችንን የነካውና በጣምም የተደሰትንበት ነው›› ብለዋል።

የጎፋ ልዩ ዞን አስራ ሁለት ወረዳዎች ያሉት መሆኑንና በጉባዔው ላይ ከአስራ አንድ ወረዳዎች የተወጣጡ አንድ መቶ ሃያ አንድ አመራሮች፣ ሰማንያ ዘጠኝ አደራጆችና አባላት በጠቅላላው 210 ተሳታፊዎች መገኘታቸውን አቶ እንድርያስ ጠቅሰዋል። ወረዳዎቹም 1ኛ, ሳውላ ከንቲባ፣ 2ኛ, ደምባ ጎፋ, 3ኛ, ኡባ ደብረ ፀሃይ፣ 4ኛ, ወይዳ ልዩ ወረዳ፣ 5ኛ, ማሎ ኮዛ ፣ 6ኛ, ሰሜን አሪ፣ 7ኛ, ገዜ ጎፋ፣ 8ኛ,

ባስኬቶ ልዩ ወረዳ፣ 9ኛ, ዛላ ወረዳ፣ 10ኛ, ደራ ማሎ፣ 11ኛ, ኡባ እና 12ኛ, ቁጫ ወረዳዎች ሲሆኑ በዕለቱ የቁጫ ወረዳ ተወካዮች በዕክል ምክንያት በጉባዔው ሊሳተፉ አለመቻላቸውን አስታውቀዋል። ጉባዔው በአቶ እንድርያስ ኤሮ መኖሪያ ቤት ግቢ ውስጥ ለጉባዔው ተብሎ በተዘጋጀ ዳስ ውስጥ መከናወኑን ከሥፍራው የተገኘው ዜና ያስረዳል።

የጎፋ ልዩ ዞን ስድስት ነጥቦች ያሉት የአቋም መግለጫ በማውጣት ተጠናቋል። እነሱም÷

1. የገዥው ፓርቲ በአባሎቻችንና በደጋፊዎቻችን ላይ እየደረሰ ያለው ግድያ፣ እስራት፣ ድብደባ፣ ዛቻ፣ ከመሬት ማፈናቀል እንዲሁም ሌሎች አፈናና እንግልቶች እንዲቆሙ እንጠይቃለን። በመላው ኢትዮጵያ የሚደርሱ ተመሳሳይ ችግሮችንም በጥብቅ እንቃወማለን፤ እናወግዛለንም።

2. በሃገራችን የፍትህ፣ የነፃነትና የዕኩልነት ሥርዓት እንዲሰፍን እንጠይቃለን። ለተግባራዊነቱም በሰላማዊ መንገድ የያዝነው ትግል ግብ እስከሚመታ ድረስ እንቀጥላለን።

3. በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በግልጽ በአባሎቻችንና በአመራሮቻችን በምደባ፣ በዝውውርና በደረጃ ዕድገት የሚደርሱ አድሎአዊ አሠራሮች ይቁሙ እንላለን።

4. በተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች ላይ እየተፈፀመ ያለው የዲሞክራሲያዊ መብቶች አረገጣ እንዲቆም አጥብቀን እንጠይቃለን።

5. ዜጎች የመደራጀት፣ የመሰብሰብና ሃሳብን በነፃነት የመግለጽ ህገ መንግሥታዊ መብታቸው እንዲከበር እንጠይቃለን።

6. ከህዝብ የተጣለብንን ታላቅ አደራ በጊዜያዊ ችግርና መከራ ሳንበገር ከግቡ ለማድረስ የሰላም ቀበቶ ታጥቀን በታማኝነትና በጀግንነት የተነሳን መሆናችንን ደግመን ደጋግመን እናረጋግጣለን።

**አንዲት ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!!**